ቸሁ፡እንዲህ ስ፡ያለ፡ሐሳብስ
ለምን፡በልባችሁ፡ይወጣል፡ይ
፵፱ ወርዳል፨እኔ፡እንደሆንሁ፡እጄ
ንና፡እግሬን፡እዩ፡ለእኔ፡ያለኝ
ንም፡እንደ፡አያችሁ፡ለመንፈ
ስ፡ሥጋና፡አጥንት፡የለውምና
፶ ዳስሳችሁ፡እዩኝ፨ይህንንም፡
ብሎ፡እጆቹንና፡እግሩን፡አሳያቸ
፶፩ ው፨መዝ፡፳፪፡፲፯፨ከደስታ
ም፡የተነሣ፡ገና፡ሳያምኑ፡ያስ
ብሉ አቸው፡ሲደነቁ፡ከዚህ፡እ
ንደቸ፡የሚበላ፡አላችሁን፡አላ
፶፪ ቸው፨እነርሱ ቸውም፡የተጠ
በሰ፡የዓሣ፡ግማሽና፡የማር፡
፶፫ ወለላ፡ሰጡ፨ዮሐ፡፳፩፡፲፫ ተቀ
፶፬ ብሎም፡በፊታቸው፡በላ፨ይህ
ም፡ከእናንተ፡ጋራ፡ሳለሁ፡በ‹
ሙሴ፡ኦሪት፡በነቢያት፡በመ
ዝሙርም፡ስለእኔ፡የተጻፈው፡
ሁሉ፡ይፈጸም፡ዘንድ፡አለው፡
ብዬ፡የነገርኋችሁ ቃሌ፡ነው
አላቸው፨መዝ፡፲፪፡፳፪፤፵፡፵
፩፡፳፫፡፳፫፡፳፰፤፸፡፪፡፲፤፲፫፨
፶፭ በዚያን፡ጊዜም፡መጻሕፍትን፡
ያስተውሉ፡ዘንድ፡አእምሮአቸ
ውን፡ገለጸላቸው፨የሐዋ፡፲፪፡
፶፮ ፲፮፨አላቸውም፡ኢየሱስ መከራ፡
እንዲቀበል፡በሶስተኛውም፡ቀ
ን፡ከሙታን፡እንዲነሣ፡እንዲሁ
ተጽፏል፡መዝ፳፪፤፲፫፡ኢሳ፤፶፫
፶፯ ፩፨በስሙም፡ንስሐና፡የኃጢአ
ት፡ሥርየት፡ከኢየሩሳሌም፡
ጀምሮ፡ወደ፡አሕዛብ፡ሁሉ፡ይሰ
ብክ፡ዘንድ፤ኢሳ፡፪፡፫፤ማቴ፡፳፰፡
፶፰ ፲፱፤የሐዋ፡፪፡፴፰፨እናንተም
ለዚህ፡ነገር፡ምስክሮች፡ናችሁ
፶፱ እነሆም፡እኔም፡የአባቴን፡ተስ
ፋ፡እልክላችኋለሁ፡እናንተ፡ግ
ን፡ከላይ፡ኃይልን፡እስክትለብ
ሱ፡ድረስ፡በኢየሩሳሌም፡ተቀ
መጡ፡ዮሐ፡፲፭፤፳፮፤፲፮፡፯፡የሐዋ
፷ ፩፡፬፨ወደ፡ውጭም፡እስከ፡ቢታ
ንያ፡አወጣቸው፡እጁንም፡ዘረ
ጋና፡ባረካቸው፨ዘሌዋ፡፱፡፳፪
፷፩ ሲባርካቸው፡አራቀ፡ብሎ፡ወ
ደ፡ሰማይ፡ዓረገ፨የሐዋ፡፩፡፱፡፲
፷፪ ፪፡፡እነርሱቸውም፡ሰገዱ፡ለት‹
ና፡በታላቅ፡ደስታ፡ወደ፡ኢየሩ
፷፫ ሳሌም፡ተመለሱ፨ሁልጊዜም
እግዚአብሔር ን፡እየባረኩና
እያመሰገኑ፡ኖሩ፤አሜን፨
የሉቃስ፡ወንጌል፡ተፈጸመ፨